# አሁን ምን እናድርግ?

ከይሄይስ አእምሮ

ይድረስ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ጣቢያ፡-

በቅድሚያ እንኩዋን ለ«ምርጫ 2002 በሰላም አደረሳችሁ» ብዬ እንዳልጀምር ራሴን አከላከልኩትና፤ እንግዲያውስ « እንኩዋን የኢትዮጵያ ሕዝብ በጉጉት ለተቀበለውና እንዳይኑ ብሌን በስስት ለሚያየው የኢሳት ወይም የእሳት ቴሌቪዥን ሥርጭት መጀመር በሰላም አደረሳችሁ» ማለትን ወደድኩ:: የሚያግባባን ይመስለኛል- በዚያውም እናንተን ጨምሮ ብዙ ሰው ከማስቀየም እድናለሁ:: በሙከራ ሥርጭቱ ላይ የነበሩኝን አንዳንድ ቴክኒክ ነክ ሂሶችን በኢሜል አድራሻችሁ ሰድጃለሁ:: በማንኛውም ውጥን የሥራ ሂደት ላይ እንደሚያጋጥም ሁሉ በኢሳትም ይታዩ የነበሩና አሁንም ቢሆን ሊኖሩ የሚችሉ ቴክኒካዊ ችግሮች የሚጠበቁ ናቸው:: በነገራችን ላይ ኢሳት ከተጀመረ ወዲህ የዲሽ ዋጋ ክፉኛ ማሻቀቡን ሰምታችሁዋል? ከብር 400 በላይ ጨምሯል:: አንዳንድ ያገራችን ነጋዴዎች (አንዳንድ ልበል እንጂ ባንድ ምሽት ከሥንቱ ጋር ተጣልቼ ዘልቀዋለሁ) እንደኢሕአዴግ በገንዘብ ፍቅር ተለክፈውብን ኅሊናቸውን ስለሳቱ የወገናቸው ዕንግልት ሊሰማቸው አልቻለም:: ክፉ ቀን መጣብንና የሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ትዝብት እያተረፈብን ወገን ለወገን ተቀራርጠናል፤ ብቻ አንድዬ ይሁነን እንጂ የኛስ ኑሮ ቴዲ አፍሮ «መላም የለው» እንዳለው ሆኖብናል::

እንደኢትዮጵያዊ ዜግነቴ በነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ የህመም ጣር ላይ ለምትገኘው ሀገሬ በሌላው አቅም ባይኖረኝ «በርቱ ተበራቱ» እያልኩ የሞራል ድጋፌን ብሰጥ አስተዋፅዖየን የምትቀበሉኝ ይመስለኛል:: አሁን ምርጫው በሰላም አልፏል- እሰዬው:: በምርጫው ሳቢያ በምንም ዓይነት መሣሪያ የማይለካ አእምሮኣዊና ኅሊናዊ ኪሳራ ቢገጥመንም የአሁኑ ከቀደመው የግንቦት 97 ምርጫ ጋር ሲወዳደር ያን ያህል የጎላ ቁሳዊና አካላዊ ጉዳት አልደረሰብንም:: የሕይዎት መጥፋት ኪሳራ በአንድ ዜጋችን ላይ ይቅርና እንደሀገራዊ ክብርና ብሔራዊ ስሜት የአንድም እንስሳ ሕይዎት መጥፋትም ቢሆን የሚያስቆጭ በመሆኑ በዚህ ለይስሙላነት እንኩዋን በማይመጥን የምርጫ ግርግር ሰበብ ክቡር ሕይዎታቸውንና ውድ ንብረታቸውን ላጡ ወገኖቻችን በግሌ የተሰማኝን አዘኔታ በአክብሮት ልገልጽ እፈልጋለሁ:: ይህን ብዬም አላበቃም::

በአሁኑ ወቅት ስለወያኔ/ኢሕአዴግ ማንነትና ታሪካዊ ተልዕኮ መነጋገር ጉንጭን ማልፋት ነው:: በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከዚህ ወልደ-ማኪያቬሊ የሰንበት ጽንስ አጥፊ ድርጅት አንዳች መልካም ነገር ይጠብቁ የነበሩ ወገኖች ከእንግዲህ ቁርጣቸውን ሊያውቁ ይገባል:: በቃ - ጅባት ብለው ዕርማቸውን ያውጡ:: ከአሁን በሁዋላ ወያኔን ማመን ጉም መዝገን መሆኑን አንድም ሰው ሳይቀር መገንዘብ ይኖርበታል:: የበሬው እንትን ይወድቅልኛል ብላ በሬው እበረቱ እስኪገባና ባለቤቱ በቁዝምዝም እስኪያሳድዳት የተከተለቺውን ቀበሮ ይመስል ድምራቸው ከ60 የሚበልጥ ወያኔ የጠፈጠፋቸው አሻንጉሊቶችና እውነተኛ የመወዳደሪያ መደላድል ያለ መስሎኣቸው ዕድላቸውን የሞከሩ ጥቂት የሕዝብን ጥያቄ ያነገቡ ፓርቲዎች ሰሞኑን «ተወዳድረው» መጨረሻቸውን አይተናል::

ይህን ምርጫ አስመልክቶ የሚያሳዝነው ሌላው ነገር ወያኔ የከሰከሰው በብዙ ሚሊዮኖች የሚገመተው የሀገር ሀብትና ገንዘብ ነው:: በሰሞኑ የሪፖርተር ጋዜጣ ላይ እንዳነበብኩት ወያኔ ለዚህ ምንም ዓይነት ብስለት ላልታየበት የተጭበረበረ ምርጫ 189 ሚሊን ብር አውጥቶኣል - ብስለት የሌለበትና የተጭበረበረ ያልኩት እኔ መሆኔ ይታወቅልኝ:: ወያኔ አንድ ፓርቲ ሆኖ ሳለ ይህን ሁሉ ገንዘብ ያወጣው በጉልበት ይ፟ት የሚገኘውን የመንግሥትነት ሥልጣን ተጠቅሞ ነው:: በገንዘቡ መጠን ላይ ግን ጥያቄ አለኝ- ከተጠቀሰው ከዕጥፍ በላይ ይበልጣል ባይ ነኝ:: የናቱን ግት እንደጠገበ ጥጃ እንዳፈተተው የሚፈነጥዝበትን የሀገር ኢኮኖሚ ጥቂት የሥልጣን ወንበሮችን ለማስጠበቅ ከሚከሰክሰው ድህነትን ለመቅረፍ ቢያውለው ሥንት ሥራ በተከናወነበት? የኢየሱስ ክርስቶስን ግምጃ ቤት ሹምን እንዳያስመስልብኝ እንጂ ይህ ጦሙን ከሚያድር ሕዝብ ለዚያውም የራሱን መሞቻ ገመድ ለማጥበቅ በግዳጅ የተሰበሰበና በዕርዳታና በቡገታ የተገኘ ገንዘብ ስንት የልማት ሥራዎችን ሊሠራ በቻለ ነበር ብሎ መቆላጨት የሁሉም ጭቁን  ዜጋ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው:: በእውነቱ በርሀብና በዕርዛት ከሚማቅቅ ሕዝብ ጉሮሮ ነጥቆ በእሳት እንደማቃጠል ነው የሚቆጠር:: ሌላ ጊዜ ምርጫ የሚባል ነገር እንዳይኖር መጮህ አለብን - ወያኔ ሥልጣን ላይ ፊጥ እንዳለ የሚቆይ ከሆነ ማለቴ ነው:: ለነገሩ ለማንስ ይጮሃል? ዙሪያው ገደል እኮ ነው የሆነብን!

ከዚህ በኋላ ወያኔን በሚያውቀው ቋንቋ ማነጋገር የሚችል ኅብረ ብሔራዊ ኃይል ወደ አደባባይ ሊወጣ እስካልቻለ ድረስ የሕዝብ ሥቃይ ይወገዳል ሀገርም ከአሳፋሪው የታሪክ ስብራት ታገግማለች ማለት የዋህነት ብቻ ሳይሆን ዕብደትም ጭምር መሆኑን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ጤናማ ዜጋ ሁሉ ሊረዳው ይገባል::ታዲያ አሁን ምን ይደረግ? ለዛሬ የምለውን ልበልና ልሰናበት::

ብዙ ነገሮችን ማድረግ እንችላለን:: ትልቁ ነገር ግና ሁላችንም ራሳችንን እንፈትሽና የሥልጣን አምሮትና የዝና ጥማት ያለብን ዜጎች እኒያን መሰል ጠንቀኛ በሽታዎች ለማሰወገድ ብርቱ ጥረት እናድርግ፡- ይህ ጥረታችን እንዲሳካም አንዳንዶቻችን ኮከባችን ተቆጥሮ ወይም ክፍላችን ተሠልቶ ፈውስ የሚያስገኝልን ጠበል ዘንድ በመሄድ መጠመቅ ሊኖርብን ይችል ይሆናል፤ የአእምሮ ሀኪም የሚያያስፈልገን ልንኖር እንችል ይሆናል፤የዝርያ ከራማን መለማመን የሚኖርብን ወገኖች ልንኖርም እንችል ይሆናል፤ የታሪክ መዛግብትን ማገለባበጥና አእምሮን የሚያፋፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ማንበብ ሊኖርብን ይችል ይሆናል፤በጊዜያዊ የስሜት ፈረስ ግልቢያ በትዕቢት ተነሳስተን በከንቱ ያስቀየምናቸው ወገኖች ካሉ ዕርቅ መፍጠር ሊኖርብን ይችል ይሆናል፤ በጥቅሉ የአእምሮ ጓዳችንን አንድም ቦታ ሳይቀር በርብረን ለዘመናት ሲያላግጡብንና ለጭራቅ ገዢዎቻችን ጭዳ ሲያደርጉን የቆዩ ዕኩይ ምግባሮቻችንን ፣አመለካከቶቻችንንና አስተሳሰቦቻችንን ከነሰንኮፋቸው መንግለን በማውጣት ተመልሰው እንዳይገቡብን ልናቃጥለቸው አመዳቸውንም እንደሕንዳውያውያኑ የሬሣ አመድ ወዲያ ልንበትነው ይገባል:: እንዲህ ስናደርግ አብረን በተጓዳኝ የምንፈትሻቸው እንከኖች ወይም ባሕርያዊ

ህፀፆችም አሉ፡- ምቀኝነት፣ ጎሰኝነት፣ትዕቢተኝነት ፣ግትርነትና «ከኔ በላይ ዐዋቂ ላሳር» ባይነት፣ ትምክህተ ኝነት፣ ስንፍና፣ፍርሃት፣ወኔቢስነት፣አድርባይነት ፣ ከሃዲነት ፣ ራስ ወዳድነት፣ ሆድ አምላኪነትና ንፉግነት፣ ቀናተኝነት ፣ በቀለም የማይገራ ማይምነት፣ ፍርድን ማዛባት፣ሕዝብ ሳይሆን ጊዜ ለሾመው መሠሪ ሁሉ አጎብዳጅነትና ሌሎች እነዚህን መሰል አሉታዊ ጎኖች ሁሉ በተለይ በእኛ በኢትዮጵያውያን ላይ ገንነውና ገንግነው ስለሚገኙ «ሰው» መሆንና የሀገር ባለቤት መሆን ካማረን መፍትሔው እነዚህን አናቋሪ መጥፎ ጠባዮች አስወግደን አዲስና ፀአዳ ስብዕናን መላበስ ነው፡፡ መሣሪያችን በጃችን ውስጥ ነው የሚገኘው፡፡ በሌለች ሀገርና ካድማስ ማዶነንኳን በማይታይ ህልማዊ ሥልጣን፣ በዘምቦ ተባርቆ ገና ሊገኝ ይችል ይሆናል በሚል ታሳቢ የሥልጣን ፍርፋሪ ርስ በርስ የምንራኮት ዜጎች መንደሩን ሞልተን በምንገኝበት ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀገር ትኖረናለች ብሎ ማሰብ ላም አለኝ በሰማይ ዓይነት የልጆች ጨዋታ ነው፡፡ ይህንን ባሕርያችንን ነው ወያኔ እንክት አድርጎ እስከጥግ እየተጠቀመበት ሃያ ዓመት ሊደፍን አንድ ክረምት ብቻ የቀረው፡፡ ከዋሸሁ ልቀጣ፡፡ ደግነቱ የሥራችንንና የየጃችንን እያገኘን ነው፡፡ ‘What goes around comes around’ ይላሉ እንግልጣርኛ ተናጋሪዎች፡፡ «አንቺም ጨካኝ ነበርሽ፤ ጨካኝ አዘዘብሽ ...» የተባለውስ ለኛ ይሆን?

ለነጻነታችን ቀን መጓተት የኛው ድርሻ ከወያኔው ይበልጥ እንደሆነ እንጂ አያንስም፡፡ ዝንጀሮና ውሻ፣ ዓይጥና ድመት፣ ጅብና አህያ፣ ... ተስማምተው መኖር በጀመሩበት የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እኛ የአንድ የዘር ግንድ ቅርንጫፎች በአንዲት ሀገር ጥላ ሥር መኖር አቅቶን ዝንታለማችንን ለባዕድ ሀገር ስደትና ለሀገር ውስጥ ባርነት ተዳርገን እንኖራለን፡፡ «የማን አባት ገደል ገባ» እያልን በልጅነት ጊዜ ሕጻናትን በማደባደብ ጎርመስ ያልነው እንጫወት እንደነበረው ሁሉ ያቺን ያረጀች ያፈጀች የልጆች ጨዋታ ተጠቅሞ ወያኔ እኛን ትልልቆቹን ሲያጃጅለንና ሲያናቁረን ዝም ብለን ለዝጌሩ ሰጥተን ተውነው፡፡ የሌባ ዓይነ ደረቁ አጅሬ ወያኔ ደግሞ የባሕርይ አባቱን የሰይጣንን ግብረ አምልኮ አያጉዋድል እንጂ የኛ ሥቃይ ከማስደሰት በስተቀር አያስከፋውም፡፡ ዝምታችንን ከመጤፍ ባለመቁጠርም ሰ–ች በሰ–ች ላይ ቀርቶ ዲያቢሎስ እንኩዋን በማንም ላይ ሊሠራው የሚሰቀጥጠውን ግፍና በደል ሁሉ አናት ባናት የከምርብናል፡፡ ይህም ሊያልፍ የግድ ቢሆንም አንገታችንን መድፋታችን የልብ ልብ ሰጥቶት ይሄውና አበቅቴው እስኪያልፍ በጋለ የብረት አለንጋ ይገሸልጠናል፡፡

ለማንኛውም በዚህ እንተማመን፡- አንተ የዚህ ዘር አንተ የዚያኛው ዘር መባባልን ባቆምን ማግሥት የነጻነታችን ችቦ ይለኮሳል ኘ ባለችኝ እወራረዳለሁ፡፡ ለነገሩ «በሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል» እንዲሉ የሀገራችን ታሪካዊ ጠላቶች በመሀላችን ባሠረጉት የተረገመ ሸንት ምክንያት፣ ያም ሸንት ታሪካዊ ግዳጁን ተወጥቶ ከመድረኩ እስኪወርድ ድረስ የአሣራችን መብዛት ከዘር ጋር እንዲገናኝ ሆን ተብሎ ሤራ ተሸረበብን እንጂ በሀገራችን ውስጥ የዘር ልዩነት እንደሌለ በበኩሌ በፍጹም ልቤ አምናለሁ፡፡ እንደኔ ውሱን ግንዛቤ በዓለም ላይ ሦስት የሰው ዘር መኖሩንና በመጤነት ሳይሆን በትውልድ አፍሪካ ውስጥ አንዱ ብቻ መኖሩን ነው የምረዳው፡፡ በመሠረቱ የሰው ልጅ ዘር አንድ ነው- በዘልማድ ነጭ ወይም ጥቁር ወይም ወይባ እንላለን እንጂ፡፡ አንድ የሚያደርጉን ሥንትና የጋራ ሰብኣዊና ሀገራዊ ዕሴቶች እያሉን ጥቃቅንና ዘመን ያለፈባቸውን ሰበብ አስባቦች በማጉላት በውጤቱ መቼም የማይጠረቃ ቁሳዊና ሥነ ልቦናዊ እርካታን መሻት ጤናማነት አይደለም፡፡ በመልክ አንድ፣በቋንቋ በአብዛኛው ተቀራራቢ፣በኑሮና በባህል ተመሳሳይ ... በሆነ ሕዝብ መሀል፣ የጠላትን አጀንዳ ለማስፈጸምና በእግረ መንገድም ባቋራጭ የተገኘን ሀብትና ሥልጣን ለመቆጣጠር ልዩ ልዩ ማናቆሪያ ሸብልቆችን መቀርቀብ ከፍለው የማይጨርሱትን ዕዳ ከሰባት ትውልድም በሚያልፍ ሁኔታ ለተከታታይ ቤተሰቦች አውርሶ በቁምም በሞትም መሞት ማለት ነው - ለሚረዳው፡፡

የጥፋት ተልዕኮ ይዘው ወደዚች ዓለም በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚመጡ ሰው መሳይ ፍጡራን በየዘመናቱ ያጋጥማሉ፡፡ አነሳሴ ይይዘኛል እንጂ ወደ ኋላም ዘወር ብዬ የሀገራችንን ሁኔታ ብቃኝ ደስ ባለኝ ነበር፤ የሆነው ቢሆን ግን እንዳሁኑ ዓይነት የታሪክ ዝቅጠት ባገራችን ታይቶ እንደማይታወቅ የክሬን መመሥከር እፈልጋለሁ፡፡ እውነት ነው - ለሥልጣን ሲባል ሕዝብን መፍጀትና ሀገርን በማያባራ ጦርነት መማገድ በጣም የከፋ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ይህንንም ጨምሮ ሀገርን ሲያሻ በጅምላ ሲያሻ በችርቻሮ መቸብቸብ፣ቅንጣት የሀገር ስሜት አለመኖር ብቻ ሳይሆን የሚገዙትን ሕዝብና ሀገር እስከመጸየፍ በሚያደርስ ጥላቻ መታወር፣ለስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ሲባል አንዱን የሕዝብ ክፍል የወገኑ መስሎ እጅግ በሚያሳፍርና ከመሪ ቀርቶ ከተራ ዜጋ እንኳ በማይጠበቅ መደዴ አነጋገር « እንኩዋን ከናንተ ተፈጠርን» ብሎ በታሪክ ፊት መዋረድ፣ ያ ኩሩ ሕዝብ የተለዬ ጥቅም እንዳገኘ በማስመሰልም ከሌሎች ወገኖቹ ለመነጠል መሞከር (ለነገሩ የማያፍር ሰው ውርደትን አያውቅም) ... ከወንጀሎች ሁሉ የከፋና አንቀጽም ገና ያልተበጀለት ልዩ ወንጀል መሆን አለበት፡፡ ይህ ዓይነት ማፈሪያ በሥነ ሕይዎት ክፍለ ትምህርት እንዳነበብነው በሚሊዮን ዓመታት አንዴ በየትኛውም ጎሳ ውስጥ ሊፈጠር የሚችል የሁላችን ጉድ እንጂ የትግራይ ቅድስት ምድር ብቻዋን አትችለውም - ይከብዳታል፡፡ በሀገር ወዳድነቱ ቅንጣት የማይታማው መንግሥቱ ኃ. ማርያምም እንደዚሁ ከራስ ካሳር እስከራስ ዱሜራ በሚዘልቅ የሀገር የቆዳ ስፋት የሁላችንም ጉደ ነበር፡፡ የአንድ ዜጋ ክፋትም ሆነ በጎ ትሩፋት የሁሉም እንጂ « ሲሞቅ በማንኪያ ሲቀዘቅዝ በእጅ» እንደሚባለው ሲያፎፋ ለነሱ ሲያለማ ለኛ ብሎ ነገር ሊኖር አይገባም፡፡ እዚህ ላይ በተለይ የአትሌቲክስና በአጠቃላየ ደግሞ የሌሎች ስፖርታዊ ድሎችን እናስታውስ፡፡ ቀነኒሳና ኃይሌ ሲያሸንፉ የሚከፉ ትግርኛና ጉራግኛ ተናጋሪዎች፣ ገብረ መድኅንና ክብርት ዉኃ አጣጨ ወርቅዬ ሲያሸንፉ የሚከፉ ኦሮምኛና አማርኛ ተናጋሪዎች አጋጥመዋችሁ በዝምታ አልፋችሁ ከሆነ ሐኪም ዘንድ ባለመውሰዳችሁ ቢያንስ ትኮነናላችሁ፡፡ ግን እመኑኝ ያን ያህል የሚብስበት ታማሚ ዜጋ የለንም፡፡ ካለም ፈጣሪ በቸርነቱ እንዲያስበው በጋራ እንጸልይ፡፡ በቸር ያገናኘን፡፡